ቀን 13/09/11 ዓ.ም

ለሚመለከተው አካል በሙሉ

እኛ የ 2011 ዓ.ም. የጎንደር ዩኒቨርሲቲ ኢንተርን ሃኪሞች ታካሚዎቻችን ሆስፒታሉንና ሃኪሞችን የሚመለከቱ 9 ጥያቄዎችን በፅሁፍ እንዲሁም በ 13/08/11 በተካሄደ ሰላማዊ ሰልፍ አስተዳደሩ በተገኘበት በቀረበ የአቋም መግለጫ ካሳወቅን በኃላ የሆስፒታሉ እና የዩኒቨርስቲ አስተዳደር ጥያቄዎቻችን አግባብነት እንዳላቸው አምኖ በሁለት ሳምንት ውስጥ ችግሮችን እንደሚፈታ ቃል ገብቶ ነበር እኛም ያቀረብናቸው ጥያቄዎች ባስቸካይ ካልተፈቱ ስራችንን ለመቀጠል አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ስለሚከተን ስራ ለማቆም እንደምንገደድ አሳውቀን በአስተዳደሩ ተቀባይነት አግኝቶ ነበር ነገር ባለመቻሉ በ 25/08/11 ታካሚዎቻችን በአግባቡ አስረክበን ስራ አቁመን መውጣታችን ይታወቃል።

ጎን ለጎንም አስተዳደሩ በተከታታይ ባዘጋጃቸው ውይይቶች ሁሉ ተገኝተን ችግሮች እንዲፈቱ የመፍትሔ አካል ለመሆን ቁርጠኝነታችንን አሳውቀናል። በ 07/09/11 አዲስ አበባ በትምህርት ሚኒስቴር፣ ጤና ሚኒስቴር እና የሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር በተዘጋጀው ውይይት ተወካዮቻችንን ልከን ጥያቄዎቻችንን አሳውቀን መንግስትም ችግሮችን ለመፍታት ያቋቋመውን ግብረ ኃይል የመጨረሻ ውሳኔ በመጠባበቅ ላይ እንገኛለን።

ከዚህ አንጻር የጎንደር ዩኒቨርስቲ ሆስፒታል አስተዳደርም ያቀረብንለትን ጥያቄ በቶሎ ምላሽ ሰጥቶ ወደስራችን ገብተን ቀጣይ ትግላችንን እየሰራን መቀጠል እንደምንፈልግ በፕሬዘዳንቱ አማካኝነት ግንኙነት በማድረግ ከህ/ጤ/ሳ/ኮ አስተዳደር ውስጥ ገልያላቸው ከህክምና ት/ት ቤት ኃላፊና ከሆሲፒታሉ የቢዝነስና ልማት አስተዳደር ጋር ለሁለት ሰዓታት ያክል በየዋርዶች በመዞር መጋዘን የሚመስሉ ማደሪያዎች እንዲፀዱና አንዳንድ ተጀምረው ያሉ ህንፃዎች ባያልቁም እና እንዲሁም በተለያዩ የስራ ሙያ ውስጥ ያለን ባለሙያዎች ጥርት ያለ ስራ ክፍፍል ስሌለን እሱን በሁሉም  መኝታ ክፍሎች እና ድንገተኛ ክፍሎች ከተለጠፈልን በማንኛውም ሰዓት ወደስራ እንደምንገባ መግባባት ላይ በደረስንበት ሰዓት ሴኔቱ ያስተላለፈው ውሳኔ ግልፅ እና ወቅታዊ አለመሆኑ እናም በማግስቱ በተላለፈው ትዕዛዝ እኛ የማንፈርም ቢሆንም እንኳን የምንፈርመው የይቅርታ ደበዳቤ ግልፅ እንዲደረግልን ስንጠይቅ መልስ የሚሠጥ አካል አለመኖሩ እና የህክምና ት/ት ቤት ሀላፊው ደብዳቤውን ሊሠጥ ፈቃደኛ አለመሆኑ ሁሉም በአንድነት ሳይፈርም ወደቤቱ እንደሚሄድ በተስማማንበት ሰዓት ከጎንደር ሲቪክ ማህበራት እናግኛችሁ እና ለመባረር የተነሱበት ምክንያት ምንድነው ተብለን በመጠየቃችን በማስረዳት ላይ ባለንበት ወቅት የግቢው ፕሮክተሮቹ በታዘዙት መሠረት በየዶርሙ ውጡ ማለት ጀምረው በነበረበት ሰዓት በመሀከል የጎንደር ሲቪክ ማህበራት እና የፀጥታ ክፍል በኛ ላይ ጥቃት እንዳይደርስ ውጡ የተባላችሁበት መንገድ አግባብ አይደለም በማባሉ ለጊዜው ይቀመጡ በሚል ተስማምተው በግቢው ተወካይ ስብሰባ ተካሂዶ በዚህም ሰዓት ደብዳቤው ተነቦልን እሱም በውስጡ “በስራ ማቆማችን ግዜ የበደልነው አካል እና የስራ ባልደረቦችን ሆነ አስተዳደሮችን ይቅርታ መጠየቅ እንዳለብን፣ በማንኛውም አይነት academic decision ቢወሰን እንድንቀበል፣ ከዚህ በኃላም በእንደዚህ አይነት ተግባር ላንሠማራ በሚል ” ቃል ገብተን እንድንፈርም መሆኑ ከተነገረን በኃላ ይሄንን እንደማንፈርም እና ምንአልባት ያስቀየምንው ካለ ይቅርታ የሚጠይቅ የይግባኝ ደብዳቤ ለፕሬዘዳንት ፅ/ቤቱ አስገብተን ድጋሜ የሴኔቱን ውሳኔ በመጠባበቅ ላይ እያለን

1. ግቢው ለእኛ ውጡ ብሎ በሴኔት ካስወሰነ በኃላ የቀመጡ የሚል ሃላፊነት የመውሰድ ህጋዊ ደብዳቤ አለማስቀመጡ ጉዳዩን እቤታችን ሆነን መከታተል እንደምንችል
2. እዚህ ተቀምጠን እየተሰማን ያለው አንዳንድ ዛቻ እና ማስፈራሪያ ስለሚያስጨንቀን እና
3. ሙሉ ተማሪው የቤተሠብ መጨነቅ በመኖሩ በ 11/09/11 በተደረገልን ድርጊት የጎንደርን ህዝብና ተወካዮች የሲቪክ ማህበራት(ጎንደር አቃፊ እና የሁሉም ሀገር እንደሆነች ስላስመሰከሩ፣ ከአደጋ እንዳዳኑን ስለቆጠርን ከልብ እያመሰገንን፣ ጥያቄያችንን እስከመጨረሻው በመከታተል እንድታስጨርሱት ከወዲሁ መልዕክት ማስተላለፍ እንወዳለን። በመጨረሻም ከግቢው ምንም አይነት የተሠጠን ክሊራንስ ሳይኖር መውጣታችን እና ምንም አይነት የማባረሪያ ደብዳቤም ሆነ በተጨባጭ መዝገብ እንዴለለ የሚመለከተው አካል እንዲያውቅልን እንፈልጋለን ።

በመጨረሻም የግቢው አስተዳደሮች አሁንም ቀላል የሆኑ ጥያቆዎችን መልሶ ማስገባት እየተቻለ አሁንም ውስጥ ለውስጥ ለሲኒየር እና ለሬዚደንት የሚነገሩ አሻጥሮች ለሀገር ወይንም ለወገን አይጠቅምም። ከጀርባችንም ምንም አይነት የፖለቲካ አካል እንደሌለን እየተናገርን መልስ ላለመለስ ክፍተት መፍጠሩ ተገቢ ነው ብለን አናምንም።

ከ 2011 ተመራቂ የጎንደር ዩኒቨርሲቲ ሆስፒታል ኢንተርን ሀኪሞች

ግልባጭ

ለፕሬዘዳንት ጽ/ቤት

ለ ጎ/ዩ/ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ክሊኒካል ዳይሬክተር

ለአካዳሚክ ዳይሬክተር

ለህክምና ትምህርት ቤት

ለጤና ጥበቃ ሚኒስተር

ለክልል ጤና ጥበቃ ቢሮ

ለሁሉም ት/ት ክፍል

ለጠ/ሚ ጽ/ቤት

ለመገናኛ ብዙሃን